# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት
# ሽምግልና ለመቀመጥ የተደረገ ስምምነት

ጉዳይ: ____________________________________________________________

ዲ.ሲ. ኮድ ታይትል 16፣ ምዕራፍ 42 በሚያዘው መሰረት፣ በዚህ ሽምግልና የሚሳተፉ አካላት በሚቀጥሉት ደንቦች/ነጥቦች እና ሁኔታዎች ለመሽምገልና ለመሳተፍ ይስማማሉ፡

1. **የሽምግልና ትርጉም**: ሽምግልና ማለት ሽምጋይ፣ አካላት ጉዳያቸውን በተመለከተ በገዛ ፈቃዳቸው ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ለመርዳት ያህል ውይይት እና ድርድር እንዲያደርጉ የሚያመቻችበት ሂደት ነው።
2. **የሽምጋይ ተራ**: ሽምጋይ የህግ ምክር አይሰጥም፣ በጉዳዮች ውሳኔ አይወስንም ወይም መፍትሄ ይሆናል ብሎ የሚያምንበትን ነገር አካላት እንዲቀበሉ አያስገድድም። ሽምጋይ፣ አካላቱ ችግሮችን በመለየት፣ በውይይት ሊመጡ ለሚችሉ እንቅፋቶች በማጉደል እና አማራጭ መፍትሔዎች ፍለጋን በማሳደግ ይረዳል።
3. **ተሳትፎ በፈቃደኝነት ነው**: ተሳታፊዎች በዚህ የሽምግልና ሂደት የሚሳተፉት በክፍት አእምሮ (ጉድ ፈይዝ) መሆኑ ይስማማሉ፣ ለሚያጣላውን ነገር ለሁሉቱም አካላት ተቀባይነት ያለው መፍትሔ ለማስገኘት ከልብ የመነጨ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሽምግልናው በሂደት እያለ ማንኛውም አካል ወይም ሽምጋይ ሽምግልናው ሊያቆም ይችላል።
4. **ኮከስ**: ሽምጋይ ሽምግልናው እየተካሄደ እያለ በማንኛውም ጊዜ ከአንድ አካል ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አካላት ጋር ለየብቻ ሊገናኝና ሊወያይ ይችላል ("ኮከስ")። ለየብቻ (ኮከስ) የሚደረጉ ውይይቶች በሙሉ በምስጢር ይያዛሉ፣ ሽምጋይም ከአካላቱ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ለሌሎች ተሳታፋዎች አይናገርም።
5. **ሽምጋይ እና የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች ሚስጢራዊነት**: ሽምጋይ እና የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች የሁሉም በሽምግልና ጊዜ የሚደረጉ ውይይቶች ምስጢራዊነት ይጠብቃሉ[1]። ሽምጋይ ወይም የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች በማንኛውም የፍርድ ቤት ሂደት እንደ ምስክሮች ወይም በቃለ መሃላ ምስክርነት እንዲሰጡ የፍርድ ቤት ማዘዣ ሊሰጣቸው አይችልም።
    a. **ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፐሽንስ):**
        i. ሽምጋይ እና የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች፣ ሽምግልና እየተደረገበት ስላለ ጉዳይ በተያያዘ የሽምግልናው ማጣራት፣ ምዝገባ እና መርሐ ግብር ማስያዝ ጨምሮ በሽምግልና ሂደት ውስጥ ስለሚነሱ ወይም ከሽምግልናው ጋር በተያያዘ ስለሚደረግ ማንኛውም ውይይት በመሃከላቸው ሊካፈሉ ይችላሉ።
        ii. ሽምጋይ ወይም የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች የሽምግልና ውይይቶች ይዘታን ሊያወጡላቸው የሚችሉ ሁኔታዎች:
            1. በሽምጋዩን ወይም በሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞችን ምክኒያታዊ በሆነ እይታ ውይይቶቹ በሰው ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ቁስል ሊደርስ ይችላል ብለው እንዲያምኑ የሚያደርግ ከሆነ፣
            2. ውይይቶቹ፣ አስፈላጊ ሆኖው ከተገኙ በማንኛውም የህግ እርምጃ ሽምጋዩን ወይም የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞችን ለመከላከል የሚጠቅሙ ከሆነ፣
            3. ውይይቶቹ፣ የተንሳቀለውን ሰው ከጉስቁልና የመከላከል ሀላፊነት ላለው የህዝብ ኤጀንሲ ለመንገር የሰዎች ጉዳት፣ ቸልተኝነት፣ መተው፣ ወይም ብዝበዛን እንደ ማስረጃነት ሊጠቅሙ የሚችሉ ከሆነ፣ ወይም
            4. በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ ወይም መመሪያ መሰረት መውጣት ካለበት።
        iii. ሽምጋይ ወይም የሽምግልና ፕሮግራም ሰራተኞች ለፍርድ ቤት የሚከተለውን ይገልጻሉ፡

[1] የ"ሽምግልና ውይይት" በሽምግልና ጊዜ፣ ወይም ሽምግልናን ግምት ውስጥ ለማስገባት፣ ለማድረግ፣ ለመሳተፍ፣ ለማነሳሳት፣ ለመቀጠል ወይም እንደገና ለመገናኘት የሚነገር፣ ወይም ሽምጋይ ለመቅጠር የሚሰጥ ቃል (አፍአዊ፣ በጽሑፍ፣ የተቀዳ፣ የንግግር ወይም ንግግር አልባ) መግለጫ ነው።

1. ሽምግልና መደረጉ ወይም መቆሙ፣
2. ስምምነት ላይ መደረሱ እና አለመደረሱ፣ እና
3. ተሳታፊዎቹ እነማን እንደነበሩ

6. **<u>የተሳታፊ ሚስጢራዊነት</u>**: ተሳታፊዎች የሁሉም የሽምግልና ውይይቶች ምስጢራዊነት ይጠብቃሉ፣ በሽምግልና ሂደት ስለ ተደረጉ ውይይቶችን የድርድሩ አካላት ካልሆኑ ሰዎች ጋር አይነጋገሩም።
   a. **<u>ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ)</u>**:
      i. በሽምግልና ጊዜ የነበሩ ውይይቶችን፣ በሽምግልና ሂደት በተሳተፉ ሁሉም አካላት፣ እንዲወጡ ከተስማሙ፣ ወይም
      ii. በዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ ህግ ወይም መመሪያ የሚያስፈልግ ከሆነ።
7. **<u>ይፋ እንዳይወጣ የማድረግ ልዩ መብት (ፕሪቪሌጅ ኤገይንስት ዲስክሎዠር):</u>** በዲ.ሲ. ኮድ §16-4203 እንደተመለከተው በሽምግልና ጊዜ የሚደረጉ ውይይቶች ይፋ ያለመሆን ልዩ መብት አላቸው:
   a. **<u>ልዩ ሁኔታዎች (ኤክሰፕሽንስ):</u>**
      i. ልዩ መብቱ በዲ.ሲ. ኮድ § 16-4204 እንደተመለከተው ይጣላል ወይም ይከለከላል፣ ወይም
      ii. በዲ.ሲ. ኮድ §16-4205 እንደተዘረዘረው ልዩ መብት ተግባር ላይ የማይውልበት ልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናል።
8. **<u>አለበለዚያ ተቀባይነት የሚኖረው (አዘርዋይስ አድሚሲብል)</u>**: ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል ማስረጃ ወይም መረጃ በሽምግልና ጊዜ ስለ ታየ ወይም ስለ ተነገረ ብቻ ተቀባይነት የሌለው ወይም ከግኝት የሚከለከል አይሆንም።

ዛሬ ________ ቀን ________________ ወር፣ 20____፣ ከታች በመፈረም፣ ይሄን ስምምነት እንዳነበብኩ፣ እንደተረዳሁ እና በስምምነቱ ለመገዛት እንደተስማማሁ እውቅና እሰጣለሁ።

______________________________
ሽምጋይ

______________________________ ______________________________
አካል ጠበቃ

______________________________ ______________________________
አካል ጠበቃ

______________________________ ______________________________
አካል ጠበቃ

______________________________ ______________________________
አካል ጠበቃ